የሰ/መ/ቁ. 18832

ኅዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ጌታቸው ምህረቱ

አሰግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነገረ ፈጅ ልኡል ሰገድ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ ከበደ ቱሉ /6 ሰዎች/

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በሐረሪ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አመልካች መስሪያ ቤት ያላግባብ ከስራ ስላሰናበታቸው ሕጉ የሚፈቅድላቸውን ክፍያዎች አመልካቹ እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉ ሠራተኞች ሲሆኑ የተቀጠሩትም ለተወሰነ ጊዜ ነው፡፡ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪዎች ለአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክስ አቅርበው ከጡረታ አበል እና ከደሞዛቸው አንዱን እንዲመርጡ ተወስኖ በዚህ መሠረት ተጠይቀው ጡረታ አበሉን በመምረጣቸው ነው፡፡ ዘላቂ የጡረታ አበል ክፍያ ያለው ሠራተኛ በአ/ቁ 88/86 እና 42/85 አንቀጽ 39 መሠረት የስንብት ክፍያ አይከፈለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም በአ/ቁ 42/85 አንቀጽ 10 መሠረት የተቀጠሩ መሆናቸውን አመልካች ስላላስረዳ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው፡፡ የጡረታ አበላቸውን ስለመምረጣቸው አላስረዳም፡፡ የጡረታ አበል ያለው ሠራተኛ ተጨማሪ ስራ እንዳይሰራ አልተከለከለም፡፡ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የተለያየ ክፍያ እንዲከፈላቸው



ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የሐረሪ ከፍተኛ ፍ/ቤት መልስ ሰጪዎችን ሳይጠራ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም አላስተባበሉም፡፡ በእድሜ ምክንያት በጡረታ ስለተገለሉ ላልተወሰነ ጊዜ ሊቀጠሩ አይችሉም፡፡ የደንብ ልብስ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች በገንዘብ ተተምኖ እንዲከፈላቸው የሚፈቅድ ሕግ የለም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ተጠሪዎች የጡረታ አበላቸውን መርጠው ጡረታቸውን ወስደዋል እየተባለ ከሥራ መሰናበታቸው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ተጠሪዎች በአመልካች መ/ቤት የተቀጠሩት እድሜያቸው ለጡረታ በመድረሱ በጡረታ ከተገለሉ በኋላ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ጡረታ አንድ ሠራተኛ እድሜውን ሙሉ ብቃት ያለው ሠራተኛ ሆኖ እንደማይቀጥል ከእድሜው መግፋት ጋር የሥራ ውጤታማነቱ እንደሚቀንስ ስለሚታመን እድሜውን ሙሉ በተቀጠረበት ስራ ላይ እንዲቀጥል መደረጉ የአሰሪውን ጥቅም ይጎዳል ተብሎ ስለሚታመን ሠራተኛው ከስራ ተሰናብቶ አሰሪው ብቃት ያለው ሠራተኛ በቦታው እንዲተካ ለማስቻል ሠራተኛው በጡረታ የሚገለልበት ስርአት ነው፡፡ ተጠሪዎች በዚህ መልኩ የጡረታ እድሜአቸው ደርሶ በጡረታ የተገለሉ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በጡረታ የተገለለ ሰው ስራ መስራት አይችልም የሚባል ባይሆንም አንድ አሰሪ በጡረታ የተገለለን ሠራተኛ በድጋሚ ላልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪዎች ራሳቸው ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ለተወሰነ ጊዜ መቀጠራቸውን አምነው ለቋሚ ሠራተኛ የተጨመረው ደሞዝ ለእነሱም እንዲጨመርላቸውና በሌሎችም ጥያቄዎች ላይ ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ እንግዲህ በአንድ በኩል ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ

ጊዜ መሆኑን አምነው ሲከራከሩ የነበረ መሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ እድሜያቸው ለጡረታ ደርሶ ከስራ የተሰናበቱ መሆኑ ተዳምሮ ሲታይ አመልካች ተጠሪዎችን የቀጠረው ላልተወሰነ ጊዜ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ስለሆነ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛም የተወሰነው ጊዜ ሲያበቃ ሊሰናበት እንደሚችል በአ/ቁ. 42/85 አንቀጽ 24/1/ ተመልክቷል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለበቂ ምክንያት ከተቋረጠ ግን ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራ እስኪያቅ ቢቆይ ኖሮ ያገኝ የነበረውን ደሞዝ የሚያሕል ደሞዝ እንደሚከፈለው በአዋጁ አንቀጽ 43/4/ለ/ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎቹ ደግሞ የተሰናበቱት የውሉ ጊዜ ከማብቃቱ 15 ቀናት በፊት መሆኑን አመልካች ራሱ አምኗል፡፡ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ባደረግነው የስራ ውል ላይ በተስማማነው መሠረት በአ/ቁ. 42/85 አንቀጽ 32/2/ መሠረት የ1 ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ እችላለሁ ሲል ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን ተፈፃሚነት ያለው አመልካች የጠቀሰው አንቀጽ ሳይሆን አንቀጽ 35/2/ ሲሆን ይህም ቢሆን አመልካቹ የተወሰነው ጊዜ ሳያልቅ ውሉን ለማቋረጥ መብት አይሰጠውም ይህ ከሆነ ሠራተኞቹ ሊከፈላቸው የሚገባው ለቀሪው 15 ቀን ማግኘት የሚገባቸውን ደሞዝ ብቻ ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሐረሪ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 171/95 በታህሣሥ 12 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተጠሪዎች የሥራ ስንብት ሕገ-ወጥ ነው በማለት የካሣ ክፍያ፣ የደንብ ልብስ በገንዘብ ተቀይሮ፣ እና ክፍያ ለዘገየበት እንዲከፈላቸው የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. በሌላ በኩል ተጠሪዎች በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመት ያልተጠቀሙበት የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው እና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሠርተው ያልተከፈላቸው ቀሪ ደሞዝ እንዲከፈላቸው የሰጠው የውሣኔ ክፍል ብቻ ጸንቷል፡፡



3. አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ15 ቀን ደመዛቸውን ይክፈላቸው፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ